# መኢአድ ባዘጋጀው የመዋያያ መድረክ ላይ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ትምህርት ሰጡ።

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እሁድ ታህሳስ 22/2004 ዓ.ም. አዲስ አበባ በሚገኘው ዋናው ጽ/ቤቱ ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የፍልስፍና መምህር የሆኑት ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ደስታ ‹‹ህጋዊ አስተዳደርና የመብት ጥያቄ በኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ ትምህርት አቅርበዋል።




የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) እንዲያስተምሩ የጋበዛቸው ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ንግግራቸውን የጀመሩት ኢጣሊያዊው ኒኮሊ ማካቬሊ ያለውን እሳቸውም በመድገም ነበር፤ ማካቬሊ በነበረበት የዛሬ ስድስት መቶ ዓመት ‹‹ስለ ልዑላኑ መናገር አንገት ያስቆርጣል፤ ግን መባል ያለበት መባል አለበት።›› ብሏል፤ ካሉ በኋላ እኔም መባል ያለበትን መባል አለበት ብዬ ነው ዛሬ ንግግር የማደርገው። እናንተ ደግሞ መባል ያለበት መባል አለበት ብቻ ሳይሆን መደረግ ያለበት መደረግ አለበት ብላችሁ ነው በፓርቲያችሁ የተሰባሰባችሁት፤ ለማለት፣ ለመናገር ለመንቀሳቀስ ነፃነት ወሳኝ ነው፤ ብለዋል ምሁሩ።

ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ በገለፃቸው ላይ ገዥው ፓርቲ የዜጎችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብት እየገፈፈ ጠዋትና ማታ የሚነግረን ስለልማታዊ መንግስትነቱ መሆኑን ጠቅሰው ልማታዊ ትያትር፣ ልማታዊ ፊልም፣ ልማታዊ ዘፈን፣ ልማታዊ ባለሃብት፣ ይባስ ብሎ ልማታዊ እስረኛም መኖሩን እየነገረ እንደሚቀልድ አንስተዋል።



ምሁሩ በማብራሪያቸው ላይ ሰርአይዛ በርሊን የተባለ ሰው እንደገለፀው ሁለት ዓይነት የነፃነት ጽንሰ ሃሳቦች መኖራቸውን አንስተው አንደኛው ፖስቲቭ ፍሪደም ሲሆን ሁለተኛው ኔጋቲቭ ፍሪደም መሆናቸውን ከጠቀሱ በኋላ ፖስቲቭ ፍሪደም ሰዎች የፈለጉትን እምነት የመከተል፣ በዘራቸው የመደራጀትና የመሳሰሉት ሲሆኑ ኔጋቲቭ ፍሪደም ደግሞ ክዋኔ ላይ የሚያተኩር ነው ይላሉ። የገዥው ፓርቲ ፖስቲቭ ፍሪደም ላይ ችግር የለበትም። መብትህ ነው እንደፈለክ ሁን ይላል። ችግር ያለው በኔጋቲቭ ፍሪደም ላይ ነው። ዜጎች የመጻፍ መብት አለኝ እጽፋለሁ ሲሉ በማን ላይ ነው የምትጽፈው? የመናገር መብት አለኝ የሚል ዜጋ መናገር ሲጀምር ማንን ነው የምትናገረው? እሰበሰባለሁ ሲል በማን ላይ ነው የምትሰበሰበው? የሚል ጥያቄ ያነሳል። በማለት በኢሃዴግ መንግስት የኔጋቲቭ ፍሪደም መብቶች እንደማይሠሩ ተናግረዋል። አያይዘውም ያልኳችሁን አድርጉ፤ የማዛችሁን ፈጽሙ ከማለት ውጭ ትችትንና ምክርን የመስማትና የማስተናገድ አቅም የሌለው ሥርዓት መሆኑን አብራርተዋል።




ዶ/ር ዳኛቸው የገዥውን ፓርቲ የእኔን ብቻ ስሙኝ ባህሪ ሲያብራሩ ‹‹ የምንገነባው እኛ የምናጠፋውም እኛ፣ ከእኛ ውጭ ያለችሁት ዜጎች አያገባችሁም አፋችሁን ዝጉ የተባልንበት ዐውድ ውስጥ ነው ያለነው›› ካሉ በኋላ ከእናንተ የሚፈለገው አድናቆት መስጠት እንጂ መተቸት አይደለም ተብለናል። አፄ ኃይለሥላሴን መሬት ላራሹ ለምን አላከፋፈሉም ማለት እንደማንችለው ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትንም ከኢህአዴግ መጠበቅ የለብንም ብለዋል ዶ/ር ዳኛቸው።

ዶ/ር ዳኛቸው ስለዳኝነት ሥርዓት ሲገልጹ ማንም ሰው በራሱ ጉዳይ ዳኛ ሊሆን እንደማይገባው ነገር ግን ዘውዳዊው ሥርዓት በራሱ ጉዳይ እራሱ ይፈርድ እንደነበረና ኢህአዴግም በራሱ ጉዳይ እራሱ ዳኛ እንደሚሆን ጠቅሰዋል። ንብረትን በተመለከተም የሰዎችን ንብረት ያለፈቃዳቸው አንስቶ ለሌላ መስጠት አይቻልም፤ ኢህአዴግ ግን ደርግ ያደርገው እንደነበረ የአንዱን ንብረት ወስዶ ለሌላ ይሰጣል፤ ብለዋል። ኢህአዴግ ዘውዳዊውንና የደርግን ሥርዓት ወስዶ ራሱ ዳኛ ሆኖ ይፈርዳል።

የጸረ ሽብርተኝነት አዋጅን በተመለከተም የገዥው ፓርቲ አባላት ህጉ ከአውሮፓና ከአሜሪካ የተቀዳ ስለሆነ ምንም የሚወጣለት የለም እያሉ ደጋግመው ሲናገሩ መሰማታቸውን ዶ/ር ዳኛቸው ካነሱ በኋላ ነገር ግን በኢትዮጵያ የፀደቀውን የጸረ ሽብርተኝነት ህግ ፈረንጆቹ እራሳቸው

እየተቃወሙት መሆኑን ገልጸዋል። የፈረንጆቹን ስጋት ምክንያት ሲያስረዱም ህግ አውጭውም፣ ህግ ተርጓሚውም፣ ህግ አስፈፃሚውም በተግባር አንድ በሆነበት ሃገር ላይ የጸረ ሽብርተኝነት ህጉን መጠቀም አደገኛ መሆኑንና ተቃውሞን ማፈኛ መንገድ እንደሚሆን ሥጋታቸውን እየገለጹ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

መኢአድ ባዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ክቡር ኢንጂነር ኃይሉ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ፕሬዚዳንት፣ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች እና ሌሎች አባላት፣ የፓርቲው ደጋፊዎችና ጋዜጠኞች ተገኝተዋል።

ፕሬዚዳንቱ በሰጡት አስተያየት በመኢአድ ውስጥ የተሰባሰበው ኃይል ለትግልና ለመስዋዕትነት የተዘጋጀ መሆኑን ጠቅሰው የገጠሩ ሰው መስዋዕትነት እየከፈለ ያለበት ሁኔታ ላይ እንደሆነ ገልጸዋል።




ውይይቱን የመሩት ወ/ት መሰበወርቅ ቅጣው የመኢአድ የህዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሲሆኑ ከተሳታፊዎች የተለያዩ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል።